የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# በንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

## በቱሪዝም ሚኒስቴር የ2014 ዓ/ም ዕቅድ ላይ

## የተሰጠ ግብረ መልስ

ጥር/2014

## በንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

## በቱሪዝም ሚኒስቴር የ2014 ዓ/ም ዕቅድ ላይ

## የተሰጠ ግብረ መልስ

### መግቢያ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ በተሻሻለው የውሳኔ ሃሳብ ቁጥር 3/2014 መሰረት 11 ቋሚ ኮሚቴዎችን ያደራጀ ሲሆን የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም በዚህ መሠረት መቋቋሙ ይታወቃል፡፡ ቋሚ ኮሚቴው ከሚከታተላቸው አስፈጻሚ መ/ቤቶች አንዱ ቱሪዝም ሚኒስቴር ሲሆን ከተቋሙ የተላከውን የ2014 ዓ.ም እቅድ መሰረት በማድረግ በጥንካሬ፣ በዕጥረትና እንዲሁም ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ጉዳዮችን በመለየት የሚከተለውን ግብረ መልስ ሰጥቷል።

### በጥንካሬ የታዩ ዋና ዋና ጉዳዮች

- የ2014 እቅድን ለማቀድ የሀገሪቱን የብልጽግና ፍኖተ-ካርታ እንደመነሻነት በመውሰድ ሀገራችን የያዘችውን "የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት" የመሆን ራዕይ ለማሳካት ዘርፉ የሚጠበቅበትን ለማበርከት የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች ማድረጉና በዘርፉ መካተት የሚገባቸውን ግቦች በግልጽ ማስቀመጡ የሚበረታታ መሆኑ፣
- የቱሪዝም ኢንደስትሪው ዘላቂና አስተማማኝ እድገት እንዲኖረው ለማድረግ በዘርፉ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትን በማጎልበት መንግስት በዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከአምስቱ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ዘርፎች ምሰሶዎችን ውስጥ በመውሰድ የተለያዩ ሞዴል የመዳረሻ ፕሮጀክቶች ልማትና ዘርፉን በማነቃቃት መሰረት የሚጥል አገራዊ የህግ ማዕቀፎችን ማሻሻያ ለማድረግ ማቀዱ፣
- ከዚህ በፊት ተቋሙን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉና ጠንካራ ተቋም ገንብቶ ለቀጣይ አመታት መሰረት የሚጥሉ ስራዎችን ለመስራት መመሪያዎችና ማንዋሎችን በማዘጋጀት ወደ ተጨባጭ ስራ በመግባት እንቅፋት የነበሩትን ትኩረት በመስጠት በአጭር ጊዜ ውስጥ አቅዶ ወደ ስራ መግባቱ፣
- በሀገሪቱ ውስጥ የተፈጠረው የፖለቲካ አለመረጋጋት እና የኮቪድ 19 ወረርሽኝ የፈጠሩት ቀውሶች እያሉ በቱሪዝም ልማት ዘርፍ የቱሪዝም ገቢያን ለማሳደግ የሚያስችል እቅድን ማቀዱ የሚበረታታ መሆኑ፣

- በሁለም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ነባርና አዳዲስ ተፈጥሮአዊም ሆነ ባህላዊና ታሪካዊ መስህቦችን በወል ተለይተው እንዲታወቁና ተደራሽ እንዲሆኑ የሪሶርስ ማፒንግ (resource mapping) ስራ ከክልሎች ጋር በቅንጅትና በልዩ ትኩረት ለማከናወን ማቀዱ፣
- የሀገር ዳግም ገፅታ ግንባታ /image Rebuilding Ethiopia/ እና የአገር ውስጥ ጉብኝት ባህልን ሊያዳብሩ የሚችሉ የግብይትና ፕሮሞሽን ስራዎች ለማከናወን መታቀዱ፣
- ከነባር ክልሎች ጋር በመተባበር የቱሪዝም ዕድገቱን ለማፋጠን የሚሰራው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ ለተቋቋሙት ክልሎች ድጋፍ በማድረግ ወደ ተጨባጭ ስራ ለማስገባት ያቀደው ዕቅድ የሚበረታታ መሆኑ፣
- በዘርፉ ግልጽ የሆነ የገበያ አጋርነትንና ቀጠናዊ ትስስርን ለማጠናከር የቱሪዝም መስህብ ሀብቶችን በማስተዋወቅና ከክልሎች ጋር በቅንጅት ለመስራት መታቀዱ፤
- የተፈጥሮ ሀብትና ፓርኮች አካባቢ ከግል ባለሃብቱ ጋር በመቀናጀት ተወዳዳሪ ቱሪዝምን ለመፍጠር እቅድ መያዙ፣
- በዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢዎች ላይ ጥበቃና የሕግ ማስከበር ሥራዎችን ማሳደግን፤ ለአካባቢው ህብረተሰብ የስራ እድል በሚፈጥር መልኩ በፖሊስ ኮሌጆች በስርዓተ -ትምህርቶች ላይ ተካቶ በማሰልጠን የአቅም ግንባታ ስራን ለማሳካት መታቀዱ፣
- የሀገሪቱን የቱሪዝም ዘርፍ ለማሳደግና ተጠቃሚነትን ከፍ ለማድረግ የማስተዋወቅ የፕሮሞሽንና ግብይት ፓኬጆች፤ የብራንድ ካምፔን፤ በቱሪስት ከተሞች የሚዘጋጅ ብራንድና የዲያስፖራ ቱሪዝም ፕሮሞሽን ስርዓትን በማካተት የገበያ ልማት ስራዎችን ለመስራት መታቀዱ፣
- የ10 አመቱን የቱሪዝም ዘርፍ ዕቅዱ በታሰበዉ መንገድ ተግባራዊ ማድረግና በግንባር ቀደምነት ዘርፉን ለመምራት የሚያስፈልገዉን ሀገርዓቀፍ የቱሪዝም ፖሊሲ ክለሳ ስራ ለማከናወን መታቀዱ፡፡
- የፖሊሲ ማስፈፀሚያ የሚሆኑ የመዳረሻ ልማት ስትራቴጂ፣ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ስትራቴጂ፣ ብሄራዊ የቱሪዝም ግብይት ስትራቴጂ፣ ጋይድ ቡክ ዝግጅት፣ የፋሲል ግቢ አለም ዓቀፍ ቅርስ የስጋት ዝግጁነት ስትራቴጂ ዕቅድ ሰነድ ዝግጅት እና የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን ፖሊሲና ስትራቴጂ ማሻሻያ ደንብ ለማዘጋጀት መታቀዱ
- የቱሪዝም ፈንድ አዋጅ፣ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ አዋጅ ማሻሻያ ማጠናቀቅና ማፀደቅ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዚየም ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ማጠናቀቅ እና ማፀደቅ፣ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን የተዘጋጀ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና አሰራር ስርዓቶች

ለማዘጋጀትና ለማጸደቅ መታቀዱ በጥንካሬ የሚወሰድ ሲሆን በእጥረት የሚካተት ደግሞ እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

## በዕጥረት የታዩ ጉዳዮች

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በእቅዱ ውስጥ ቁልፍ ተግባርና በበጀት አመቱ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና ሊወሰዱ የሚችሉ መፍትሄዎቻቸውን ያላስቀመጠ መሆኑ፣
- የ2014 በጀት ዓመት እቅድ ለተቀመጡት ግቦች አመርቂ ውጤት ያላስቀመጠና የክትትልና ቁጥጥር ስራውን በተገቢው ሁኔታ ለመለካት አስቸጋሪ መሆኑ፣
- ለህዝቡና ለባለድርሻ አካላት የቱሪዝም ዘርፉን በተመለከተ ግንዛቤ ከማስጨበጥ አኳያ የተያዘው እቅድ በቂ አለመሆኑ፤
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተመደበለትን የበጀት እቅድ በየሩብ አመቱ በዝርዝር ግቦች ከፋፍሎ አለማስቀመጡ
- የተዘረፉ ቅርሶችን ከማስመለስ አኳያ ከሚመለከታቸው ባላድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ሁኔታን በእቅዱ ላይ አለመካተቱ፣
- የቱሪዝም ዘርፉ ለሀገሪቱ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ በመሆኑ የሃገሪቱ ገቢዎች በህገ-ወጦች ሳይዘረፉና ሳይጭበረበሩ በቀጥታ እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችሉ አሰራሮችና ህገ-ወጥነትን ከመከላከል አንፃር የተነደፉ በቂ ስትራቴጂዎችን በእቅዱ ላይ አለመካተታቸው፣
- በቱሪስት አካባቢዎች የሚገኙ ሆቴሎች ደረጃ አሰጣጥ ዙሪያ ባሉ ብልሹ አሰራሮችን ለመቅረፍ የተቀመጠ አሰራር በእቅድ ውስጥ አለመያዙ፣
- በእቅዱ ላይ የዱር እንስሳት የሚገኙበት ጥብቅ ቦታዎችና ፓርኮች ድንበር አወሳሰን የአካባቢውን ማህበረሰብ በሚያሳትፍ መልክ አለመታቀዱ፣
- ከቅርስ ጥበቃ አኳያ ለኢትጵያ ብሄራዊ ሙዚየም ለጥገናና እድሳት የሚወጣው ወጪና ተቋሙ የሚያስገባው ገቢ ያልተመጣጠነ፣ ሀገሪቷ ማግኘት የሚገባትን ገቢ ያላገናዘበ እና የመፍትሄ ሀሳቡም ግልፅ በሆነ ሁኔታ ተጠቅሶ አለመካተቱ ፣
- የፓርኮችና ጥብቅ ቦታዎች አከላለል የአካባቢውን ማህበረሰብ ያላሳተፈና ተገቢውን የጥናት ውጤት የሌለው መሆኑ እየታወቀ በዚህ ረገድ የአካባቢውን ማህበረሰብ አካቶ መፍትሔን ለመፈለግ የተያዘ እቅድ አለመኖሩ፣
- በበጀት የተደገፈ ስርዓተ-ፆታን ያካተተ፤ የሴቶችንና የወጣቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማሳደግና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማምጣት አቅማቸውን የሚገነቡበትና የተሻለ አፈፃፀም

በማሳየት ወደ አመራርነት ለማምጣት የሚስችል የተቀመጠ አሰራር በእቅዱ ውስጥ አለመካተቱ፣

- የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ከማሳደግና ህብረተሰቡ የቁጠባ ባህልን አዳብሮ የመጎብኘት ባህልን ከማሳደግ አኳያ ከብድር ሰጪ ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት የሚያስችል እድልን ለመፍጠር የተቀመጠ አቅጣጫ በእቅዱ ውስጥ አለመካተታቸው፣

## ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ከላይ በዕጥረት የተገመገሙ ተግባራትን ትኩረት በመስጠት በሩብ ዓመቱ በዕቅድ ተካቶ መፈጸም ያለበት ስለሆነ ትኩረት እንዲሰጠው፤

❖ ዘርፉ በአዲስ መልክ እየተደራጀ ከመሆኑ አንጻር በተለይ የሀገር ገጽታ ግንባታንና የብልጽግና ጉዞ ራዕይን ባገናዘበ መልኩ የቱሪዝምና ደጋፊ ተቋማትን የማዘመን፣ ተወዳዳሪ ቱሪዝምን በመፍጠር የመረጃ ሥርዓትን ማላቅ፣ ተቋማዊ የአቅም ግንባታን በማጠናከር የማህበረሰብ ትስስር ተጠቃሚነትን ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በማዋሀድ ከግብ ለማድረስ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያለበት መሆኑ፣

❖ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አዲስ ከመሆኑ አኳያ የራሱን የአስር አመት እቅድና የአምስት ዓመት እቅድ በማቀድ የባለድርሻ አካላትን አንቀሳቅሶ የአቅም ግንባታ ሥራን ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑ ታውቆ ትኩረት እንዲሰጠው፣

❖ ቱሪዝም በኮቪድ 19 ምክንያት በዓለምም ይሁን በሀገራችን ክፉኛ የተመታ በመሆኑ፡ በሀገራችን የፖለቲካ አለመረጋጋት መፈጠሩ ወደፊት የዓለም ሀገራት በራቸውን በመክፈት የሚችሉትን ከፍተኛ ክትትል በማድረግ ለሀገራችን የተነደፈውን ማገገሚያ ስትራቴጂ በቅርበት ድጋፍ በማድረግ መስራት ትኩረት የሚሰጠው መሆኑ፣

❖ የወደሙ ቅርሶችን መልሶ በመገንባትና ዳግም የሀገርን ገፅታ ገንብቶ ዘርፉን ለማሳደግ መስራት ልዩ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑ፣

❖ የተዘረፉ ቅርሶችን ከማስመለስ አኳያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑ፣

❖ የሀገሪቱ ትልቅ ነቀርሳ የሆነውን ሙስናን ከመቅረፍ አኳያ አስፈፃሚ መ/ቤቱ በስሩ ባሉት ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራቱ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑ፣

## ማጠቃለያ

ቱሪዝም ሚኒስቴር አሁን ላይ ችግሮችን በመለየት በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እየተሰራ ያለው ተግባር ተስፋ ሰጭ ቢሆንም በሀገራችን የቱሪዝም ኢንዱስትሪው በኮቪድ 19 በሽታና በፖለቲካ አለመረጋጋቱ ክፉኛ የተመታ በመሆኑ ሀገራችን ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆንና የሚገጥመንን ችግር ቀድሞ በመገንዘብ የመፍትሄ አቅጣጫ እያስቀመጡ በመሄድ የወቅቱ ዋነኛ ትኩረት መሆን ይኖርበታል።

በሌላ በኩል በእቅዱ ላይ በጥንካሬ የተጠቀሱትን የበለጠ በማዳበር በዕጥረት የተገመገሙትን በዕቅዱ ውስጥ በማካተት ሊፈጸሙ የሚችሉበትን መንገድ በማመቻቸት በትኩረት ሊሰራባቸው ይገባል፡፡ የተጠቀሱትን ነጥቦች ፈጥኖ ወደ ተግባራዊ አፈጻጸም በመግባት የተፈጠሩ ችግሮች ፈጥነው እንዲስተካከሉ ቋሚ ኮሚቴው ይህንን ግብረ መልስ ሰጥቷል።